# ምጥ እንዲመጣ መገፋፋት

the women's
the royal women's hospital
victoria australia

አንድ ሴት ምጥ እንዲጀምራት የሚረዳ ሰው ሰራሽ ዘዴዎችን መጠቀሙ አንዳንዴ አስፈላጊ ነው። ይህ ምጥ እንዲመጣ መገፋፋትተብሎ ይጠራል።

## ምጥ እንዲመጣ መገፋፋት ምንድ ነው?

በአብዛኛው እርግዝናዎች ላይ ምጥ የሚጀምረው በተፈጥሮ በ37 እና 42 ሳምንታት መካከል ባለው ጊዜ ሲሆን፣ ህጻኑ እንዲወለድ ይመራል። ሀኪሞችና አዋላጅ ነርሶች ምጡ በሰው ሰራሽ እንዲጀምር በሚያበረታቱበት ጊዜ ምጡ 'እንዲመጣ ይገፋፋል/induced'።

## ምጥ እንዲመጣ መገፋፋቱ ለምንድ ነው የተመረጠ?

ምጥ እንዲመጣ መገፋቱ በአብዛኛው የተለመዱ ምክንያቶች:

- እርግዝናው ከ41 ሳምንታት በላይ ከሆነው
- ሽንት ውሃ ከፈሰሰ ነገር ግን በተፈጥሮ የምጥ መኮማተር አለመጀመር
- ህጻኑ ደህና ካልሆነ ወይም በደንብ እያደገ ካልሆነ
- እናት የሆነ የጤና ጉዳይ ካለባት ነው።

## የሆኑ ችግሮች አሉን?

ምጥ እንዲመጣ መገፋፋት ጋር በተዛመደ የሚከሰቱ ችግሮች አሉ። አንዳንድ ሴቶች ምጥ እንዲመጣ ግፊት እንዲደረግ እንደማይፈልጉና የተፈጥሮ ምጥ መጀመር ላለመጀመሩ 'መቆየትና ማየትን' ይመርጣሉ።

ምጥ እንዲመጣ መገፋፋት በሚነገርበት ጊዜ ከሚቀጥለው እርግዝናዎት ጋር በተዛመደ ችግሮች እንዳሉም ነው።

ውሳኔ ከማካሄድዎ በፊት የርስዎ ሀኪም ወይም አዋላጅ ነርስ ምጥ እንዲመጣ መገፋፋት በማካሄድ ባለማካሄድ ስለሚከሰቱ ችግሮች ማብራሪያ ይሰጣሉ።

## እንዴት ምጥ እንዲመጣ ግፊት ይደረጋል?

ምጥ እንዲመጣ የሚያደርጉ አራት የተለያዩ ዘዴዎች አሉ:

- ፕሮስታግላንዲን/prostaglandin
- የሚነፋ ለስላሳ ቱኛ/a balloon catheter
- በሰው ሰራሽ የሽንት ውሃ እንዲፈስ ማድረግ
- ሆርሞንስ/oxytocin ይሆናል።

አብዛኞች ሴቶች ከመውለዳቸው በፊት እነዚህን የተቀላቀሉ መውሰድ ይፈልጋሉ።

## ምጥ እንዲመጣ ግፊት በሚደረግበት ቀን ምን ይፈጠራል?

የርስዎ ምጥ እንዲመጣ ግፊት በሚደረግበት ቀን ቀደም ሲል የነበረዎትን ዘዴ ለመለወጥ መወሰን ይቻል ይሆናል። የሴት ብልት ከተመረመረ በኋላ በርስዎ ማህጸን ጫፍ ላይ ለውጥ ካለ፣ ይህም ማለት በበለጠ ተስማሚ የሆነ ሌላ ምጥ እንዲመጣ የሚገፋፋ ዘዴ ካለ ነው። የርስዎ ሀኪም ወይም አዋላጅ ነርስ ስለዚህ ከርስዎ ጋር ይነጋገራሉ።

### ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?

አንዴ ምጥ እንዲመጣ ግፊት ከተጀመረ በቀጣይ ተደጋጋሚ ክትትል ይደረግልዎታል። በአካባቢው እግር ጉዞ መሄድ ይችላሉ ነገር ግን ከሆስፒታል መውጣት የለብዎም። የርስዎ ማህጸን ጫፍ እድገት እያሳየ ለመሆኑ ለማጣራት በተደጋጋሚ ምርመራ ይካሄዳል። ምጥ እንዲመጣ ግፊት ፈጣን የአሰራር ሂደት አይደለም። አንዴ ከተጀመረ ህጻኑ እስኪወለድ ድረስ ከ24 ሰዓታት በላይ ሊወስድ ይችላል። የርስዎ ማህጸን ጫፍ መስተካከል ካስፈለገው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቀናት ሊወስድ ይችላል።

### ምጥ እንዲመጣ ግፊቱ ከተጀመረ በኋላ ሃሳብዎን መቀየር ይችላሉን?

አንዴ ምጥ እንዲመጣ ግፊቱ ከተጀመረ በኋላ ልጅዎ እስኪወለድ ድረስ እንደሚቀጥል ይገመታል። የምጥ ማምጫ ግፊት ሂደት እንዲቆም አንመክርም።

### ከተፈጥሮ ምጥ ጋር ሲነጻጸር የበለጠ ያማልን?

እያንዳንዱ የወሊድ ምጥ ይለያያል። ለአንዳንድ ሴቶች ምጥ እንዲመጣ ግፊቱ በራሱ ከጀመረ መደበኛ ምጥ ጋር ሲነጻጸር በበለጠ ህመም እንደሚፈጥር ሲሆን ይሁን እንጂ ለሁሉም ሴቶች ላይ ይህ ትክክል አይደለም። አስፈላጊ ከሁነ ምን ጊዜም በአከርካሪ የሚሰጥ ማደንዘዣ/Epidurals ይቀርባል።

### ይህ ይሰራልን?

አንዳንድ ጊዜ ምጥ ማምጫ ግፊት እንደማይሰራና ወደ ወሊድ ምጥ መሄድ አይችሉም። ይህ ሁኔታ ከተፈጠረና ደህንነት ያላቸው ሁሉም አማራጮች ከተሞከሩ ታዲያ የቀዶ ጥገና/caesarean ሊያስፈልግዎት ይችል ይሆናል።

Watch our short video about induction of labour at https://youtu.be/sQq-PS-7Ao

## ምጥ እንዲመጣ መገፋፋት ዘዴዎች

እርስዎ የሚፈልጉት ምጥ ማምጫ ግፊት ዘዴ ምጥ ለመጀመር እንደ የርስዎ ማህጸን ጫፍ (የማህጸንዎ አንገት) ምን ያህል ዝግጁ መሆን ይወሰናል። የርስዎ ሀኪም ወይም አዋላጅ ነርስ የርስዎን ማህጸን ጫፍ ለማጣራት የብልት ምርመራ በማካሄድ የትኛው ዘዴ ለርስዎ ትክክለኛ ስለመሆኑ ያነጋግራሉ።

የርስዎ ማህጸን ጫፍ ለምጥ ዝግጁ ካልሆነ 'ማበረታቻ/Priming' ሊያስፈልግዎት ይችላል። ማበረታቻው/ Priming የሚረዳው የርስዎ ማህጸን ጫፍ ለምጥ ዝግጁ እንዲሆንና ይህም በሚነፋ ለስላሳ ቱኛ/balloon catheter ወይም ፕሮስታግላንዲን/prostaglandin በመጠቀም ማካሄድ ይቻላል።

እነዚህ ዘዴዎች የሚረዱት የርስዎ ማህጸን ጫፍ ለምጥ ዝግጁ እንዲሆን ነገር ግን ብዙዲዜ ምጥ እንዲጀምር አያደርግም።

ማበረታቻ/ Priming ከ 6 እስከ 48 ሰዓታት ባለው ጊዜ መውሰድ ይቻላል። አንዴ የርስዎ ማህጸን ጫፍ ከተከፈተ፤ ሊያስፈልግዎት የሚችል:

- የርስዎ ሽንት ውሃ እንዲፈስ እና
- ኦክሲቶሲን/oxytocin መድሃኒት፤ ይህም የምጥ መኮመታተር ይጀምራል።

ወደ ምጥ ከመግባትዎና ልጅ ከመውለድዎ በፊት እነዚህ ሁለቱንም ሊያስፈልግዎት ይችላል።

## ፕሮስታግላንዲንProstaglandin

ፕሮስታግላንዲንProstaglandin በቅባት/ጀል ወይም በክኒና መልክ ሲቀርብ፤ ይህም በርስዎ ብልት ውስጥ በማስገባት የማህጸን ጫፍ እንዲለሰልስና ለሚቀጥለው የምጥ ደረጃ ዝግጁ እንዲሆን ይረዳል።

ፕሮስታግላንዲንProstaglandin በሚደረግበት ጊዜ ቢያንስ ለ30 ደቂቃዎች የሚሆን መጋደም እንዳለብዎትና ምጥ እስኪጀምር ድረስ በሆስፒታል ውስጥ ይቆያሉ።

### ማወቅ ያለብዎት ነገሮች

- ፕሮስታግላንዲንProstaglandin አንዳንዴ የብልት ህመምን ይፈጥራል።
- በቁጥር አነስተኛ በሆኑ ሴቶች ላይ አንዳንድ ችግሮች ሲያጋጥማቸው ማለት እንደ ማቅለሽለሽ፣ ማስታወክ ወይም ተቅማጥ ይሆናል።
- ፕሮስታግላንዲንProstaglandin አልፎ አልፎ ማህጸን በጣም እንዲኮማተር ምክንያት ሊሆን ይችላል። ይህ ሁኔታ ከተከሰተ፤ ለማህጸንዎ ማዝናኛ የሚሆን መድሃኒት ይሰጥዎታል።
- ብዙዎች ሴቶች ወደ ወሊድ ምጥ ለመሄድ የበለጠ እርዳታ ያስፈልጋቸዋል።

## የሚነፋ ለስላሳ ቱኛ/Balloon catheter

ቀጭን ቱቦ ካተተር/ catheter ተብሎ ሲጠራ፤ ከቱኛ መጨረሻን በርስዎ ብልት ውስጥ ተደርጎ ወደ የርስዎ ማህጸን ጫፍ በማስገባት ከዚያም ቱኛው ከውሃ ጋር ይነፋል። ይህ የሚነፋ ለስላሳ ቱኛ/balloon catheter እንደሚባልና በርስዎ ማህጸን ጫፍ ላይ ግፊት እንዲያደርግ ይጠቅማል። የማህጸን ጫፍ እንዲከፈት በመርዳት ለሚቀጥለው የወሊድ ምጥ ደረጃ ዝግጁ ያደርጋል።

ካተተር/catheter የሚቀመጠው እስከ 12 ሰዓታት ሲሆን ከዚያም ከቱኛ ውሃው ከተወሰደ በኋላ ካተተሩ/catheter ይወጣል። ካተተሩ/catheter ውስጥ በተቀመጠበት ጊዜ በአካባቢው መደበኛ እንቅስቃሴ ማድረግ ይችላሉ።

ካተተሩ/catheter ከወጣ በኋላ ቀጣዩን እርምጃ ለመወሰን ሌላ የብልት ምርመራ ይኖርዎታል።

### ማወቅ ያለብዎት ነገሮች

- ብዙዎች ሴቶች ወደ ወሊድ ምጥ ለመሄድ በበለጠ እርዳታ ያስፈልጋል።

## ሰው ሰራሽ ለወለቀ/ለተበላሸ ህብረ ህዋሳት (ARM)

ይህ የአሰራር ሂደት በተለምዶ የርስዎ ሽንት ውሃ መፍሰስ ተብሎ ይጠራል።

አንዴ የማህጸን ጫፍ ብብቃት ሲከፈት፤ የርስዎ ሀኪም ወይም አዋላጅ ነርስ አነስ ተኛ መንጠቆ ያለውን መሳሪያ በመጠቀም የርስዎ ሽንት ውሃ እንዲፈስ ይደረጋል። ይህን በማካሄድ ጉዳት የለውም ነገር ግን ምርመራው አመቺ ላይሆን ይችላል። በርስዎ ወሊድ ምጥ ባለው ጊዜ የርስዎ ውሃ በመጠኑም ቢሆን መፍሰሱን ይቀጥላል።

### ማወቅ ያለብዎት ነገሮች

- ምንም እንኳን የርስዎ ሽንት ውሃ በቀጥታ ቢፈስም፤ የኢትብት መዛባት፤ መድማትና የበሽታ ብክለትን ሊጨምር ይችላል። ይህንን ለማስወገድ የርስዎ ሀኪም ወይም አዋላጅ ነርስ እንክብካቤ ያካሂዳሉ ነገር ግን ሊፈጠር ስለሚችል ማንኛውም ድንገተኛ ችግር ላይ ስልጠና ያገኙ ናቸው።
- የርስዎ ሽንት ውሃ በመፍሰስ የወሊድ ምጥ መጀመሩ አነስተኛ ነው። የርስዎ ሽንት ውሃ ከፈሰሰ በኋላ ቶሎ ብሎ ኦክሲቶሲን/oxytocin መድሃኒት መጀመሩ በጣም ጥሩ ነው።

## ኦክሲቶሲን/oxytocin

ይህ መድሃኒት በተፈጥሮ ወደ ወሊድ ምጥ እንዲሄዱ ከሚያደርገው ሆርሞን ጋር ተመሳሳይ ነው። በቬን ደም ስራ ውስጥ መርፌ ማስገባትና ከኦክሲቶሲን/ oxytocin የያዘ ጠብታ ጋር ማያያዝ።

ለሚሰጥዎት የኦክሲቶሲን/oxytocin መድሃኒት መጠን በመንፊያ መቆጣጠር። እርስዎ በወሊድ ምጥ እስካሉበት ጊዜ በየ ግማሽ ሰዓታት በአዋላጅ ነርስ በኩል የጠብታ መንፊያው ይከፈታል። ለዚህ የሚወስደው ጊዜ ርዝመት እንደ እያንዳንዱ ሴት ይለያያል ነገር ግን ብዙ ሰዓታት ሊወስድ ይችላል።

ጠብታው በሚካሄድበት ጊዜ በአብዛኛው አዋላጅ ነርስ ከርስዎ ጋር ይቆያል። የወሊድ ምጥ በሚካሄድበት ጊዜ የ CTG መሳሪያ በመጠቀም የርስዎን ህጻን ልብ ትርታ ቁጥጥር/ክትትል ይደረጋል።

### ማወቅ ያለብዎት ነገሮች

- በሚወስዱት ጠብታ እና CTG መሳሪያ ሳቢያ ያለዎት የአካባቢ መንቀሳቀስ ችሎታ የተወሰነ ነው።
- አልፎ አልፎ ኦክሲቶሲን/oxytocin ለማህጸን በጣም የመኮማተር ምክንያት ሊሆን ይችላል። ይህ ሁኔታ ከተከሰተ፤ በግራ ጎንዎ ገደም እንዲሉ ይጠየቃሉ ታዲያ ጠብታው ይስተካከላል ወይም ይቆማል። የማህጸን መኮማተር ችግሩን ለመቀነስ ሌላ መድሃኒት ሊሰጥ ይችላል። ይህ ሊካሄድ የሚችለው በልጅዎ ልብ ትርታ ላይ አሳሳቢ ሁኔታዎች ካለ ነው። ከእነዚህ ጉዳዮች ጋር በተዛመደ ለማካሄድ የእኛ ሀኪሞች ወይም አዋላጅ ነርሶች ሰልጥነዋል።
- የርስዎ ምጥ እንዲመጣ መገፋፊያ በኦክሲቶሲን/oxytocin መድሃኒት ጋር ከሆን በሽንት ውሃ መፍሰስ መውለድ አይችሉም።

# በሴቶች ላይ ምጥ እንዲመጣ መገፋፊያ የሚወስዱ ከሆነ

## ምጥ እንዲመጣ መገፋፊያ በሚወስዱበት ቀን

**እባክዎ በተጠቀሰው ጊዜ መድረስ።**

- ከዘገዩ፤ የርስዎ ምጥ እንዲመጣ መገፋፊያ ቀጠሮ ለሌላ ጊዜ ሊራዘም ይችላል።
- ቀደም ብሎ በመድረስ ቀደም ብለው ይታያሉ ማለት አይደለም።

ወደ ሆስፒታል እንዲገቡ ከተደረገ በኋላ በርስዎ ሀኪም ወይም አዋላጅ ነርስ የሚደረግ፡

- የርስዎን ማህጸን ጫፍ ለመገምገም የብልት ምርመራ ይደረጋል
- የልጅዎን አቀማመጥ ቅርጽ ማጣራት
- የልጅዎን ልብ ትርታ ለመከታተል መቆጣጠሪያ መጠቀም።

የብልት ምርመራ ማካሄዱ የሚረዳው ለርስዎ ሀኪም ወይም አዋላጅ ነርስ የርስዎ ማህጸን ጫፍ ለወሊድ ምጥ ምን ያህል ዝግጁ እንደሆነ ለመወሰን ነው። ከዚያም የትኛው ምጥ እንዲመጣ መገፋፊያ ዘዴ ለርስዎ ተስማሚ ስለመሆኑ ያነጋግራሉ።

የርስዎ ምጥ እንዲመጣ መገፋፊያ የሚጀመረው ሆስፒታል ከገቡ በአንድ ሰዓት ውስጥ እንደሆነ፤ ይሁን እንጂ ሆስፒታሉ በጣም ስራ ከበዛበት ሊዘገይ ወይም ለሌላ ጊዜ ቀጠሮ ይደረጋል።

በመዘግየቱ ሊያበሳጭዎት እንደሚችል ቢረዳንም ነገር ግን ለርስዎና ልጅዎት በጣም ጥሩ የሆነ እንክብካቤ መስጠት ስለምንፈልግ ታዲያ እርስዎን በሚገባ መንከባከብ የሚችል ሰው ከሌለ የርስዎን ምጥ እንዲመጣ መገፋፊያ ስራን አንጀምርም። በየጊዜው ያለውን ሁኔታ እንደምናሳውቅና መዘግየቱ በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ እንዲሆን የተቻለንን እናደርጋለን።

## የርስዎ ምጥ እንዲመጣ መገፋፊያ የሚወስዱበት ሰዓትና ቀን (Time and date of your induction)

ቀን: ..........................................................................................
(Date)

የሚደረስበት ሰዓት: ..........................................................................
(Time to arrive)

የት እንደሚኬድ: ..............................................................................
(Where to go)

የታቀደ ምጥ እንዲመጣ መገፋፊያ ዘዴ
(Proposed induction method)፡

..........................................................................................................

የርስዎን ቀጠሮ ቀንና ሰዓት በስልክ ደውለን እናሳውቃለን። አንዳንዴ እነዚህን ለሌላ ጊዜ ቀጠሮ ለማስያዝ ያስፈልገን ይሆናል።

## እኛን ለማነጋገር

ስለርስዎ ምጥ እንዲመጣ መገፋፊያ ዘዴ ለአዋላጅ ነርስ ለማነጋገር

- ፓርክቪል/Parkville: ስልክ፡ (03) 8345 2170
  ከሰኞ እስከ ዓርብ (ከጥዋት ሰዓት 8.30am እስከ ከሰዓት በኋላ 4.30pm)
- ሳንድሪንግሃም/Sandringham: ስልክ፡ (03) 9076 1245
  ከሰኞ እስከ እሁድ (24 ሰዓታት)

**የክህደት ቃል** ይህ የመረጃ ዝርዝር ወረቀት ለአጠቃላይ መረጃ ብቻ ተብሎ የቀረበ ነው። ስለልጅዎ እና የርስዎ ጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ለየት ያለ ምክር ለማግኘት ከርስዎ የጤና ባለሙያ ምክር ማግኘት አለቦት። በዚህ የመረጃ ዝርዝር ወረቀት ላይ ተመርኩዞ ለሚከሰት ማንኛውም ጥፋት ወይም ለሚነሳ ጉዳት በሮያል ሴቶች ሆስፒታል በኩል ተቀባይነት አይኖረውም። ለእርስዎ ወይም ለህልጅዎት በአስቸኳይ ህክምና እንዲደረግልዎት ከፈለጉ፤ እባክዎ በአቅራቢያዎ ያለን የድንገተኛ ህክምና ክፍል ያነጋግሩ። © The Royal Women's Hospital 2018